# ጥያቄ መልዕክት ሲሆን

ከጎዳንው

የዶ/ር ብርሃኑ ነጋን "አመርቂ ውጤት ለማግኘት አስቦ መንቀሳቀስ፡ ስለ ዴሞክራሲ ትግል አንዳንድ ጥያቄዎች።" የሚለውን ባለዘጠኝ ገፅ ጽሁፍ በጥሞና አንብቤውዋለሁ። ጽሁፋቸው ሦስት ክፍል ሲኖረው በመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍሎች ስለ ሰላሙና የአምጽ የትግል ስልት ላይ የተነሱ ጥያቄዎች ሲሆኑ ሦስተኛው ክፍል ደግሞ በብሄር የትግል ጥያዌዎች ላይ ያተኩራል። ወደ ጽሁፋቸው ጠለቅ ብዬ ከመግባቴ በፊት ግን ገና ከጅምሩ ለምን ይህን ፅሁፍ በተለይም ባሁኑ ወቅት ለመጻፍ ተቸገሩ?

ጽሁፉን ለሚያነበው ምናልባት ብዙ ትያቄዎች ባምሮው ቢመላለስ ብቻውን አይደለምና መገረም አይገባውም። በኔም አእምሮ ብዙ ነገሮችን አሰላስያለሁ። ብዙ ያስገረሙኝ ነጥቦችን አስተውያለሁ። ከሁሉም በላይ ጽሁፉ **ስለአሉባልታና ውሸት** ትኩረት ሰጥቶ የመጀመሪያውን የመግቢያ አንቀጽ ላይ አስፍረውታል። እጅግ ያስገረሙኝና ተደጋግመው በጽሁፉ የሚጠቀሱት ሁለት ጉዳዮች **"ባጭር ጊዜ"** ና **"ባነስተኛ ወጭ"** የሚሉትቃላቶች ናቸው። ሶስቱም ማለትም አሉባልታ÷ አነስተኛ ውጭና፤ ባጭር ጊዜ የሚሉት ጉዳዮች በጸሃፊው አእምሮ ውስጥ ብዙ የሚብላሉ ግን ወደፊት በግልጽ የሚያወጧቸው የጽንሰ-ሃሳብ ምልክቶች ይንጸባረቃሉ። አሉባልታው ቢገባኝም ባጭር ጊዜና ባነስተኛ ወጭ የሚሉት ግን አልጣሙኝም። ባጋጣሚ የተሰነዘሩ ናችው እንዳልል ክብደት ተሰጥተዋቸው በየ አንቀጹ ተጠቅሰዋል።

ጸሃፊው ላነሱት የራሳቸው ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት እየጣሩ እንደሆነም ጠቁመዋል። ምርምርም እያደረጉ ነው ማለት ነው። እውነታቸውን ከሆነ ይገርመኛል ምክንያቱም ያስቀመጡት ጥያቄዎች በሙሉ ድሮ ድሮ በማያሻማ መልኩ በአንጋፋ የፖለቲካ ድርጅቶች ተመልሰዋል። ብዙ ድርጅቶች በተለይም በማይወዱት ግን ነበርኩበት የሚሉት ኢሕአፓ በፕሮግራሙ ላይ እንኳን ለዶክተርና ለድሮ አሉ ቀርቶ ማንበብ ወይም መስማት የሚችል ምስኪን ገበሬም ያውቀዋል። ለጠየቁአቸው ጥያቄዎች ጸሃፊው መልስ ፍለጋ ጫካ መግባት የለበትም።

ገና በመጀመሪያ የጽሁፋቸው አንቀጽ እንዲህ ይላሉ÷ "**...ይህ አሁን ፖለቲካችንን ቀፍድዶ ከያዘው የአሉባልታና የውሸት አባዜ መላቀቅ እንዳለበት...**" ባጭሩ ሃሜትና አሉባልታ ትግሉን ጎድውታል ለማለት ነው። በኔ አመለካከትና ባብዛኛው ኢትዮጵያዊ ግንዛቤ ፖለቲካውን የቀፈደድው አንዳኛ በመንግስትነት ቁብ ያለብን ወያኔ ነው። ሁለተኛ ድርጅቶች ወይ ተባበሩ አለያም ተሰባበሩ የሚለውን የህዝብ መልእክት ድርጅቶች የገባቸው ባለመሆኑና ሶስተኛ ከመተባበር ይልቅ አፍራሽ የሆነ የአንጃነት ፀባይ ሲሆን ለዚሁም የጸሃፊው እጅ በዚህ ተግባር ስለመኖሩ የቅንጅትን የቅርብ ታሪክ ማየቱ በቂ ይመስለኛል።

ስለ መንግስት ስልጣንም ያነሱት ጥያቄዎች÷ "**...በአገራችን በአሁን ጊዜ የሚደረገው ትግል የፖለቲካ ስልጣኑን ማን ይያዘው የሚል ትግል ሳይሆን የፖለቲካ ስልጣን እንዴት ይያዛል**?፡ በማንና በእንዴት መካከል ያለ ጥያቄ ነው። ጥያቄአቸው "*የትም ፍጭው ብቻ ዱቄቱን አምጭው*" ይመስላል ምክንያቱም ጸሃፊው መጠየቅ ያለበት ..ስልጣን እንዴት ይያዛል? በማለት መጠየቃቸው ለምሳሌው የሚጥም ነው። ለኔ ግን ትኩረት የምሰጠው ስልጣን ላይ የሚወጣው መንግስት (ድርጅት) እንደደርግና እንደወያኔ ሌላውን የሚያገል ወይም በዲሞክራሲያዊ መንገድ ህዝብናና አገርን የሚያስተዳድር ስለመሆኑ ጥንቃቄ ከማድረጉ ላይ ነው። ማለትም መጠንቀቅ ያለብንና መጠየቅ ያለበት ጸሃፊው ያሳነሱት ስልጣኑን ማን ይይዛል የሚለው መሆን አለበት።

ጸሃፊው "**....ከዚህ ጋር በተያያዘም የዚህ አይነት ሰርአት ለማምጣት የሚደረግ ትግል የጥቂት ሰዎች ትግል ሳይሆን የነፃነቱ ተጠቃሚ የሆነው ሁሉ አስተዋፅኦ የማድረግ የሞራል ግዴታ አለበት...**" ሙሉ በሙሉ ያስማማናል። ግን በርግጥ በዚህ አነጋገር ካሙኑ ቀደም ሲል ህብረቱን መግፋት፤ "ዘመናዊ" ያልሆኑትን ድርጅቶች ማግለል ብሎም ወጣቱና ያረጀው በማለት መከፋፈል ጸሃፊው ካሉበት ጎራ ለምን ተንፀባረቀ? ከህዝብ ለሚሰባብሰበው ገንዘብ ለቅንጅት 70 ከመቶ ለህብረቱ 30 ከመቶ የሚለው ታዲያ ለምን ተነሳ ጥሪዎ ሁሉም ለትግሉ አስተዋጻኦ መስጠት አለበት ካለ? ወይስ ይህን ግማሽ ኢትዮጵያ ሙሉ ኢትዮጵያ የሚለውን የረከሰ አባባል አልሰሙትም ነበር?

"**...የዴሞክራሲ ትግላችን የታለመለትን ግብ በአጭር ጊዜ እንዲመታ ..**"÷ "**....ይህ የትግል ስልት በአጭር ጊዜን በአነስተኛ ወጭ ውጤት ..**"÷ "**..በትጥቅ የሚደረግ ትግል በአጭር ጊዜ የመንግስት ለውጥ..**" የጸሃፊውን መልእክት ልብ ለሚለው ችኮላ፤ጥድፊያ፤ ግልቢያ መንፈስ መታየቱ ሲሆን ፈጥኖ ድልን መቀናጀት የሚቻል ከሆነ ማንም አይጠላውም። የሆነ ሆኖ ግን ትግል መራራ፤ ውጣ ውረድ ያለውና እልህ አስጨራሽና ረጅም መሆኑን ስተው ዛሬውኑ በትረመንግስት የመጨበጥ የበረታ ጉጉት ይነበብበታል። የቸኮለ አፍሶ ለቀም ነው ነገሩ የሚመስለኝ። የሩሲያ ሰዎች እንዲህ ይላሉ "Hurry is good only for catching flies* ይህ አይነቱ ምኞት አደገኛ ነው ምክንያቱም የድሉ ቀን በተራዘመ መጠን በተለያ ባድርባዩና በአበላባዩ ላይ ከፍተኛ ቀቢጸ ተስፋ በመፍጠር የወደዱትን ትግል በመካድ ከህዝብ ጠላትነት ጎራ ያሰልፋቸዋል። ምናልባትም የአንጃዎች መፈጠር በተለይም በቅርቡ ከኢሕአፓ የፈረጠጠው አንጃ ትግሉ ረዘመ የሚል ጨለምተኛነት

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ተሸንፈው አቋራጭ መንገድ(አጭር) ለመፈለግ በመፈለጉ ሰለመሆኑ መጠራጠር የለብንም። የርሶም አንጃ ከዚህ ሃቅ የወጣ አይደለም።

**“ቅንጅት የሰላማዊ ትግል አማራጭን ሲወስድ ከግምት ያስገባቸው ስሌቶች ነበሩ። (ለምሳሌ ኢህአዴግ (ወያኔ) ይህንን ሊቀበል ይችላል በውጭ ግፊትም ቢሆን፤ ይህ የትግል ስልት በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ወጭ ውጤት ያስገኛል፤ ክዚህ ስልት ውጪ ያለው የአመፅ አማራጭ ውጤት ቢያስገኝ እንኳን ወጭው ከፍተኛ ነው፤ ውጤቱም (ዴሞክራሲ ማምጣቱ) አጠራጣሪ ነው።”** ይላሉ ጸሃፊው።/ስርዝ የኔ/ በሌላ አነጋገር ወያኔ የቅንጅትን ሃሳብ ይቀበላል፥ የውጭ ሃይሎች ( ወዳጆቹ አሜሪካንና ኢንግሊዝ ..) ተፅእኖ ያደርጉበታል የሚል ተመክሮንና ያላካተተ ምስኪንነት ነበር ማለት ነው። ተው ይህ አይበጅም ያሉ ነበሩ እኮ። ይህ አጭር ጊዜና አነስተኛ ወጭ የሚለው የጸሃፊው ሃሳብ ብዙም አልገባኝም ። ከሰላማዊ የትግል ስልት ውጭ ማለትም የትጥቅ ትግሉ ዴሞክራሲን ማምጣቱን የተጠራጠሩት ወያኔንና ሻዕቢያን እንደማስረጃ በመውሰድ ይመስለኛል። ግምቱ ትክክል ቢሆንም መሳሪያ ያነሳን ሁሉ እንደሻቢያና ወያኔ ማስቀመጡ ቢያንስ ቢያንስ ስህተት ነው።

ጸሃፊው የወያኔን አምባገነንነት ለማስረዳት ለምን ቀንደኛ ወያኔ የነበረውን(ምናልባትም አሁንም የሆነውን) **ስዬ አብርሃምን** ግፍ የተፈፀመበት አድርጎ ማቅረቡ ነው። የስዬን ሰውነት ከፍ ለማድረግ ሁለቱን ሃቀኛ ኢትዮጵያውያን ማለትም ዳንኤልንና ነፃነትን ለጠቀሱ ከማይገባቸው ቦታ አስቀምጠዋቸዋል። ዶህና ይሁን ግን ከእስር ቤት ስትፈቱ እነዳንኤልም እንዲፈቱ አሳስበው ነበር? “ወዳጅ ሲያረጅ በጓሮ ይሄዳል” እንደሚባለው ካልሆነ በስተቀር አባል ነበርኩበት ከሚሉት የድሮ ድርጅቶ ማለትም ኢሕአፓ ወያኔ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ በእሰር የሚማቅቁትን የአመራሩን አባላት እነ ደብተራውን ከስዬ ይልቅ ማንሳቱ አይመረጥም ብለው ይሆን?

ጸሃፊው ቢያውቁትም ባያውቁትም ወይም ቢያምኑበትም ባያምኑበትም በኢትዮጵያችን በመፈክርና በተግባር ኢሕአፓ ከጥንት ከመሰረቱ የሚታገልበትን ሁል-ገብ የትግል ስልት ሃቀኛ የሆኑ ድርጅቶች ሁሉ በፕሮግራማቸው ውስጥ አካትተው መታገል አለባቸው። ሁለ-ገብ የትግል ስልት በተለይ የሰላሙ ትግል የሚቻል ከሆነ በሰላሙ መስክ ለመታገል የማይፈልግ ጤነኛ ድርጅት አለብዬ አላስብም። ወያኔ በጠመንጃ አፈ-ሙዝ ስልጣን ላይ መውጣቱ ለጸሃፊው ካልተዘነጋ በስተቀር ይህን ነብሰበላ መንግስት እንዴት በሰላሙ ትግል ልናሰናብተው ይቻላና ብለው አሰቡት? የተመክሮ ባለፀጋ ድርጅቶች ወያኔን በሰላማዊ መንገድ መገርሰስ የማይቻል መሆኑን ሲናገሩ ለምን አልተደመጡም? ለውደፊት ግን የተመክሮ ባለጸጋ ከሆኑት መማሩ ተገቢ ለመሆኑ ለጸሃፊው ለማሳመን አልሞክርም። ፖሊሶች እንዲህ የሚል አባባል አላቸው “The afternoon knows what the morning never expected."

በብሄርም የተደራጁ ድርጅቶች በዲሞክራሲ ግንባታው ውስጥ ስለሚኖራቸው አወንታዊና አሉታዊ ውጤት መልስ የሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች በጸሃፊው ተቀምጠዋል። ላነሱአቸው ጥያቄዎች ድርጅቶ AFD ውስጥ ሲዘፈቅ ያውም የኢትዮጵያ ስም እንዳይነሳ፥ ባንዲራዋም እንዳይውለበለብ ሲደረግ ከመቃወም ይልቅ ሲደግፉትና ሲከራከሩለት አይተን ልባችን ደምቷል። ካነሱት አልቀረ በዛሬው የኢትዮጵያ ሁኔት አንገብጋቢው ጥያቄ የዲሞክራሲ እንጂ የብሄር አይደለም። በብሄር ጥያቄ ዙሪያ መሳሪ እንስተው የሚታገሉ ድርጅቶች ትግላቸው ከወያኔ ከሆነ ሊበረታታ ሲገባ ጠባቸው ግን ከኢትዮጵያ ጋር ከሆነ ሸውደን ማለፍ ከሃቀኛ የኢትዮጵያ ልጆች የማይጠበቅ ቅሌት ነው። በተለይ በሻቢያ ነፃ አውጭነት ሰር መሰባሰብ ማሞቂሎ መሆን ነው።

በመጨረሻ ለማለት የምፈልገው የጸሃፊው ሙከራ በወቅታዊና አታጋይ በሆኑ ሃሳቦች ላይ ሆኖ ቢሆን ኑሮ ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር። በተለይም ስለ የጋር ትግል (ህብረት)። የወቅቱ ጥያቄ መሆን ያለበት ሃቀኛ የኢትዮጵያ ድርጅቶች እንደት መሰባሰብ አለባቸው? አንጃንነትን እንዴት እንዋጋ? .. . የመሳሰሉት መሆን አለባቸው!!!

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com